# የሐዲስ ኪዳን

# መጻሕፍት

# መክፈቻ

★

-- *Ex Libris* --
B. N. Lapsley
375 Willow Wood
Murphy, Texas 75094

የቃለ ሕይወት ሥነ ጽሑፍ ድርጅት
ፖ. ሣ. ቁ. 127
አዲስ አበባ ።

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| ስለ አራቱ ወንጌላት | 3 |
| የማቴዎስ ወንጌል | 4 |
| የማርቆስ ወንጌል | 5 |
| የሉቃስ ወንጌል | 6 |
| የዮሐንስ ወንጌል | 7 |
| የሐዋርያት ሥራ | 8 |
| የጳውሎስ የሕይወት ታሪክ ባጭሩ | 9 |
| የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች (ካርታ) | 10 |
| የጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች | 11 |
| መጀመሪያይቱ የጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች | 12 |
| ሁለተኛይቱ የጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች | 13 |
| የጳውሎስ መልእክት ወደ ገላትያ ሰዎች | 14 |
| የጳውሎስ መልእክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች | 15 |
| የጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች | 16 |
| የጳውሎስ መልእክት ወደ ቆላስይስ ሰዎች | 17 |
| መጀመሪያይቱ የጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች | 18 |
| ሁለተኛይቱ የጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች | 19 |
| መጀመሪያይቱ የጳውሎስ መልእክት ወደ ጢሞቴዎስ | 20 |
| ሁለተኛይቱ የጳውሎስ መልእክት ወደ ጢሞቴዎስ | 21 |
| የጳውሎስ መልእክት ወደ ቲቶ | 22 |
| የጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልሞና | 22 |
| ዕብራውያን | 23 |
| መጀመሪያይቱ የጴጥሮስ መልእክት | 24 |
| ሁለተኛይቱ የጴጥሮስ መልእክት | 25 |
| መጀመሪያይቱ የዮሐንስ መልእክት | 26 |
| ሁለተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት | 26 |
| ሦስተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት | 27 |
| የሐዋርያው የያዕቆብ መልእክት | 28 |
| የያዕቆብ ወንድም የይሁዳ መልእክት | 29 |
| የዮሐንስ ራእይ | 30 |
| የዮሐንስ ራእይ (ካርታ) | 31 |
| ቅድስት ሐገር (ካርታ) | 32 |

# ስለ አራቱ ወንጌላት

የወንጌሎች መልእክት የተደረሰው መንፈስ ቅዱስ ለዚህ ሥራ በመረጣቸው በአራት ሰዎች ነው ። ከእነዚህ ሰዎች ሁለቱ ማለት ማቴዎስና ዮሐንስ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ነበሩ ። ቅዱስ ሉቃስ በሕክምና በማገልገል የጳውሎስ ተከታይ ስለነበር ፤ ከእርሱ የሰማውን የወንጌል መልእክት ጻፈ ። ይህም የሆነበት ቅዱስ ጳውሎስ ወንጌልን የሰማው ከክርስቶስ በመሆኑ ነው (ገላ. 1 . 12) ። ቅዱስ ማርቆስ ደግሞ ከሐዋርያ ጴጥሮስ ጋር በሮም እንደ ነበረ ሲታወስ የወንጌልን መልእክት ከእርሱ እንደተቀበለ ይታመናል (1 ጴጥ. 5 . 13) ። በሥራ በኩል ማቴዎስ ቀራጭ ፤ ሉቃስ ሐኪም ፤ ዮሐንስ ዓሣ አጥማጅ ሲሆኑ ፤ ማርቆስ ግን ገና ወጣት ስለነበር ሌላ ሥራ ሳይዝ የክርስቶስን መንገድ ተከተለ ።

ከላይ እንደተመለከተው ሁሉ አራቱ ደራሲዎች በሥራ ፤ በጊዜ ፤ በቦታ የተለያዩ እንደ መሆናቸው መጠን ፤ ወንጌሎቻቸውም የተለያዩ ዓላማዎች ነበሩዋቸው ። ማቴዎስ ወንጌሉን በተለይ ለአይሁድ ጽፎ ስለ ነበር ከዚሁ የተነሣ ኢየሱስ ክርስቶስ የትንቢት ፍጻሜና የአይሁድ ንጉሥ ወይም መሲህ መሆኑን ለማረጋገጥ ባደረገው ጥረት ፤ በመደጋገም ጥቅሶችን ከብሉያት አመልክቶአል ። ቅዱስ ማርቆስ ለሕዝብ በጻፈው ወንጌሉ ላይ ክርስቶስ ኃጢአት የሌለበት ፍጹም የእግዚአብሔር ብላቴና እንደሆነ ያስረዳል ። ከዚሁም ጋር የአይሁድን ባሕልና አስተያየት በሚያወሳበት ወቅት በጣም እየተጠነቀቀ ነው ። ሉቃስ ሐኪም እንደመሆኑ መጠን የታሪኩን ትልም ቴዎፍሎስ ለተባለ ለሮም ሊቅ አቅርቦአል ። የእርሱ ወንጌል በተለይ ለተማሩት የተዘጋጀ ስለነበር ዋና ዓላማው የክርስቶስን ቸርነትና ፍቅር ለመግለጽ ነበር ። የዮሐንስ ዓላማ ደግሞ በወንጌሉ መጨረሻ ግድም እንደተገለጠው አንባቢዎቹ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሞት ወደ ሕይወት እንዲሻገሩ ነው (20 . 30—31) ። ክርስቶስ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ እንደሆነ በዚሁ ወንጌል ተገልጠአል ።

# የማቴዎስ ወንጌል

ስለ ደራሲው ፤

የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ክርስቶስ ለደቀ መዝሙርነት ሲጠራው ቤቱንና ሥራውን ትቶ የተከተለው ፤ የሌዊ ወገን የነበረው ቀረጭ ነው (ማቴ. 9 . 9 ፤ ማር. 2 . 14)።

የተጻፈበት ጊዜ ፤ በ60 ዓ. ም. ግድም ።

ዓላማው ፤

ማቴዎስ ይህን መጽሐፍ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ሲጽፍ ፣ ክርስቶስ በልደቱ ፣ በሕይወቱ ፣ በሞቱና በትንሣኤው የብሉይ ኪዳንን ትንቢቶች እንደፈጸመ ለማረጋገጥ ነው።

አይነተኛ ጥቅስ ፤

ማቴዎስ 3 . 2

«መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ።»

አይነተኛ ቃላት ፤

መንግሥተ ሰማያት

## አስተዋጽዎ


መግቢያ ፤

| | |
|---|---|
| ስለ ኢየሱስ ልደትና አስተዳደግ | 1 . 1—2 . 23 |
| ስለ ጥምቀቱና ፈተናው | 3 . 1—4 . 25 |

የክርስቶስ ትምህርትና ምግባር ፤

| | |
|---|---|
| ስለ እግዚአብሔር ጽድቅ አይሁዶችን እንዳስተማረ | 5 . 1—7 . 29 |
| ሕሙማንን እንደፈወሰ | 8 . 1—9 . 38 |
| ስለ መንግሥተ ሰማያት ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ | 10 . 1—13 . 58 |
| ሕዝቡን እንደመገበና በውኃ ላይ እንደተራመደ | 14 . 1—17 . 27 |
| ስለ ትሕትናና ስለ ዓለም ፍጻሜም ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ | 18 . 1—25 . 46 |

ሕማማቱ ፤

| | |
|---|---|
| ኢየሱስ ተይዞ ሲፈረድበትና ሲሰቀል | 26 . 1—27 . 66 |
| የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ | 28 . 1—20 |

# የማርቆስ ወንጌል

ስለ ደራሲው ፤

በአንደኛ ጴጥሮስ 5 ፡ 13 እንደተመለከተው ማርቆስ ወደ ክርስትና ሃይማኖት የተመራው በጴጥሮስ አማካይነት ነበር ። ስለሆነም ከጴጥሮስ የሰማውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ታሪክ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ጻፈው ። ማርቆስ ጳውሎስን በአንደኛው ጉዞው እንደተከተለውና በሮምም አብሮት እንደነበር ይታወሳል ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

የማርቆስ ወንጌል ከአራቱ ወንጌላት መጀመሪያ የተጻፈ ሲሆን ጊዜውም በ55 ዓ. ም. ግድም ነው ።

ዓላማው ፤ ይህ መልእክት የተዘጋጀው በተለይ ለአሕዛብ ነው ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤

በማርቆስ 15 ፡ 39 የምናገኘው ከሮማዊው መቶ አለቃ አንደበት የፈለቀው ድምጸ አንክሮ ነው ። «ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ ። »

አይነተኛ ቃል ፤ «ወዲያውም»

## አስተዋጽዎ

መቅድም ፤

| | |
|---|---|
| ስለ ኢየሱስ ጥምቀትና ስለ ፈተናው | 1 . 1—13 |

ኢየሱስ በገሊላ ሲሰብክ ፤

| | |
|---|---|
| ደቀ መዛሙርቱን እንደመረጠ | 1 . 14—3 . 19 |
| በምሳሌ እንዳስተማረ | 3 . 20—4 . 41 |
| በሚያስተምርበት ወቅት ሕሙማንን እንደፈወሰ | 5 . 1—8 . 26 |
| ስለ ሕማማቱና ስለ ሞቱ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ | 8 . 27—9 . 50 |

ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገው ጉዞ ፤

| | |
|---|---|
| በይሁዳ እንዳስተማረ | 10 . 1—45 |
| በኢያሪኮ ዓይነ ሥውሩን እንደፈወሰ | 10 . 46—52 |

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሕማማት ፤

| | |
|---|---|
| ወደ ኢየሩሳሌም እንደገባ | 11 . 1—12—44 |
| ስለ ዓለም ፍጻሜ እንዳስተማረ | 13 . 1—37 |
| የጌታ እራትና የጌቴሴማኒ ጸሎት | 14 . 1—42 |
| ክርስቶስ እንደተያዘ | 14 . 43—15 . 14 |
| ክርስቶስ እንደተሰቀለ ፣ እንደሞተና እንደተቀበረ | 15 . 15—47 |
| ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ | 16 . 1—20 |

# የሉቃስ ወንጌል

ስለ ደራሲው ፡

ቅዱስ ሉቃስ ከጳውሎስ የሰማውን ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ጽፎ አል ። ቅዱስ ጳውሎስ ወንጌልን የተማረው ከክርስቶስ መሆኑ ይታወሳል ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

ሉቃስ መልእክቱን የጻፈው ጳውሎስ በቄሳርያ ታስሮ በነበረበት ጊዜ እንደሆነ ይገመታል ። (57—58 ዓ. ም.) ።

ዓላማው ፤

በመጽሐፉ መጀመሪያ ምዕራፍ በቍጥር ሦስት ላይ እንደተመለከተው ፣ መጽሐፉ በመጀመሪያ ቴዎፍሎስ ለተባለ የግሪክ ሰው ተልኰአል ። ምንም እንኳ ቴዎፍሎስ የግሪክ ሰው ቢሆን የሮም መንግሥት ባለ ሥልጣን እንደመሆኑ መጠን የሉቃስ ወንጌል የተዘጋጀው ለሰለጠነው የሮም ሕዝብ እንደሆነ ይገመታል ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ ሉቃስ 1 . 4

«ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «ስርየት»

## አስተዋጽዎ


መግቢያ ፤

ስለ ክርስቶስ ልደትና አስተዳደግ 1 . 1—2 . 52

ስለ ጥምቀቱና ፈተናው 3 . 1—4 . 44

ክርስቶስ በገሊላ እንዳስተማረ ፤

የደቀ መዛሙርቱ መጠራት 5 . 1—6 . 16

ሕዝቡን እንዳስተማረና ሕመምተኞችን እንደፈወሰ 6 . 17—9 . 50

ክርስቶስ በይሁዳና በሰማርያ በነበረበት ወቅት ፤

ሕዝቡን አስተማረ 9 . 51—11 . 54

በትምህርቱ የተጠቀሱ ምሳሌዎች 12 . 1—16 . 31

ስለ እምነት የሰጠው አስተያየት 17 . 1—19 . 27

ስለ ክርስቶስ ሕማማት ፤

ኢየሩሳሌም ገብቶ እንዳስተማረ 19 . 28—21 . 38

የጌታ እራት ፣ የጌቴሴማኒ ጸሎትና የይሁዳ ክህደት 22 . 1—46

ተይዞ ለፍርድ እንደቀረበ 22 . 47—23 . 25

እንደተሰቀለ እንደሞተና እንደተቀበረ 23 . 26—56

የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ 24 . 1—53

# የዮሐንስ ወንጌል

ስለ ደራሲው ፤

የዚህ መልእክት ደራሲ ቅዱስ ዮሐንስ መሆኑ የተረጋገጠ ነው። ይሁን እንጂ ደራሲው በድርሰቱ ውስጥ ስሙን «ዮሐንስ» ብሎ ከመጥቀስ ይልቅ «ኢየሱስ ይወደው የነበረ ደቀ መዝሙር» በማለት ሊያመለክት ይፈልጋል። ይኸውም እርሱ በጣም ኃጢአተኛ ሳለ ክርስቶስ እንደወደደው በማስታወስ ነው።

የተጻፈበት ጊዜ ፤ ከ65 ዓ. ም. እስከ 70 ዓ. ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።

ዓላማው ፤

የመጽሐፉ ዋና ዓላማ ከዚህ በታች ዓይነተኛ ጥቅስ ሆኖ የቀረበው ሐሳብ ነው።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ ዮሐንስ 20 . 31

«ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ ፣ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል።»

አይነተኛ ቃላት ፤ ብርሃንና ሕይወት

## አስተዋጽዎ


መግቢያ ፤

ስለ እግዚአብሔር ቃል 1 . 1—14

ስድስቱ ተዓምራት ፤

የዮሐንስ ምስክርነትና ውኃ ወደ ወይን ጠጅ መለወጥ 1 . 15—2 . 12

የአይሁድን መኳንንት እንደተቃወመና ፤ የአረማዊውን ሹም ልጅ እንደፈወሰ 2 . 13—4 . 54

ሽባው ሰው እንደተፈወሰ 5 . 1—47

ስለ ሕይወት እንጀራ ፣ አምስት ሺህ ሰዎች መመገብ 6 . 1—71

የዳስ በዓል ፣ የዓይነ ሥውሩ መፈወስ 7 . 1—10 . 21

የመቅደስ መታደስ በዓል ፣ የዓልአዛር ከሞት መነሣት 10 . 22—11 . 54

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሕማማት ፤

መግቢያ 11 . 55—12 . 11

እሑድ ፣ ወደ ኢየሩሳሌም እንደገባ 12 . 12—36

ረቡዕ ፣ በይሁዳ የደረሰበት መቃወም 12 . 37—50

ሐሙስ ፣ የጌታ እራት 13 . 1—14 . 31

በጌቴሴማኒ ሲሄድ የተደረገ ውይይት 15 . 1—17 . 26

መያዝና ለፍርድ መቅረብ 18 . 1—27

ዓርብ ፣ ጲላጦስ ሲፈርድበት 18 . 28—19 . 16

እንደተሰቀለ እንደሞተና እንደተቀበረ 19 . 17—42

እሑድ ፣ የክርስቶስ ትንሣኤ ፤ ደቀ መዛሙርቱን ሲያስተምራቸው 20 . 1—21 . 25

# የሐዋርያት ሥራ

ስለ ደራሲው ፤

ይህን የቤተ ክርስቲያን እድገት ታሪክ ሉቃስ የጻፈው የወንጌሉን ታሪክ በማ ስከተል ነው ። ሁለቱም መልእክቶች የተጻፉት ቴዎፍሎስ ለተባለ ሰው ነው ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን የጻፈው ከጳውሎስ ጋር በሮም በነበረበት ጊዜ ነው ። (59—6 ዓ. ም.) ።

ዓላማው ፤

የመልእክቱ ዋና ዓላማ የክርስቶስ ተከታዮች በተለይም ጴጥሮስና ጳውሎስ ፤ የክርስቶስን ትዕዛዝ በመፈጸም ወንጌልን እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ እንደሰበኩ የሚያ ሳይ ነው ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ የሐዋርያት ሥራ 1 . 8

«ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «ኃይል»

## አስተዋጽዎ


የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በኢየሩሳሌም ሳሉ ፤

| | |
|---|---|
| ከጴንጤ ቆስጤ በፊት | 1 . 1—2 . 13 |
| ከጴንጤ ቆስጤ በኋላ | 2 . 14—5 . 42 |

የወንጌል መስፋፋት ፤

| | |
|---|---|
| ስለ እስጢፋኖስ | 6 . 1—7 . 60 |
| ስለ ፊልጶስ | 8 . 1—40 |
| ስለ ሳኦል | 9 . 1—31 |
| ስለ ጴጥሮስ | 9 . 32—12 . 25 |

በቅዱስ ጳውሎስ በኩል ወንጌል እንደተስፋፋ ፤

| | |
|---|---|
| የመጀመሪያው የጳውሎስ ጉዞ | 13 . 1—14 . 28 |
| በኢየሩሳሌም የተቋቋመ ጉባኤ | 15 . 1—35 |
| ሁለተኛው የጳውሎስ ጉዞ | 15 . 36—18 . 22 |
| ሦስተኛው የጳውሎስ ጉዞ | 18 . 23—21 . 17 |

የጳውሎስ እስራት ፤

| | |
|---|---|
| ጳውሎስ ተይዞ ሲመረመር | 21 . 18—23 . 22 |
| ጳውሎስ በቂሣርያ ታስሮ ሳለ | 23 . 23—26 . 32 |
| ወደ ሮም ሲጓዝ | 27 . 1—28 . 31 |

# የጳውሎስ ሕይወት ታሪክ ባጭሩ

የጳውሎስ ስም ሳኦል በነበረበት ጊዜ ከእለታት አንድ ቀን ከኢየሩሳሌም ወደ ደማስቆ ሲሄድ ሳለ ወደ ሰማይ አርጐ የነበረው ኢየሱስ በሚያንጸባርቅ ብርሃን ተገልጦለት ወዲያውኑ እንደ ጌታውና እንደ መድኃኒቱ ሊቀበለው ቻለ ። 35 ዓ. ም.

ከዚያም ወደ ምድረበዳ ተገልሎ ወንጌልን ከክርስቶስ ከተማረ በኋላ ወደ አንጾኪያ ሄደ ። ከዚያም ከነባርናባስ ጋር የመጀመሪያ ጉዞውን ወደ ገላትያ አድርጐ በገላትያ አብያተ ክርስቲያናት ተመሠረቱ ። ወደ አንጾኪያ በተመለሰ ጊዜ የገላትያን መልእክት ጻፈ ። 47—48 ዓ. ም.

በኢየሩሳሌም ከአሕዛብ ስለ አመኑ ሰዎች የአሪት ሕግ አጠባበቅ ክርክር ተነሥቶ ስለነበር ጳውሎስም በጉባኤው ላይ እንዲገኝ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ (49 ዓ.ም.)። ጉባኤው እንደተፈጸመ ወደ አንጾኪያ ተመለሰና ሁለተኛ ጉዞውን በመጀመር ወደ ቆሮንቶስ ሄዶ ከዚያ ወደ ተሰሎንቄ ሁለት መልእክቶች ላከ ። 50—52 ዓ. ም.

ወደ አንጾኪያ ከመመለሱ በፊት ወደ ኢየሩሳሌም ወረደ ። ቀጥሎም በሦስተኛው ጉዞ በኤፌሶን ለሁለት ዓመታት ባስተማረበት ወቅት ወደ ቆሮንቶስ የመጀመሪያውን መልእክት ጻፈ (53—54 ዓ. ም.) ። እንዲሁም ሁለተኛውን መልእክት ከማሴዶን አከታተለ ። ጉዞውን ቀጥሎ በቆሮንቶስ በደረሰ ጊዜ ከዚያ አንድ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች ላከ ። (56 ዓ. ም.)

ቅዱስ ጳውሎስ በተዘዋወረባቸው በታዎች ሁሉ ምጽዋት ከአማኞች ሰብስቦ ስለነበር ፤ ይህን የምጽዋት ገንዘብ ለኢየሩሳሌም ድሆች አማኞች ለማከፋፈል እስያን በመተው ወደ ኢየሩሳሌም አመራ (57 ዓ. ም.) ። በኢየሩሳሌም ሳለ በቤተ መቅደስ ውስጥ በተነሣው ሁከት በሮሜ ወታደሮች ተይዞ ወደ ቂሳርያ በመላክ ለሁለት ዓመታት በእስር ቤት ቆየ ። (ሉቃስ የወንጌሉን ታሪክ የጻፈው በዚሁ በቄሣርያ ከጳውሎስ ጋር በነበረበት ጊዜ እንደሆነ ይታወሳል) (57—58 ዓ. ም.)

ጳውሎስ እንደታሰረ ወደ ሮሜ ተላልፎ ስለነበር ፣ ለሁለት ዓመታት እዚያው በቆየበት ወቅት ለኤፌሶን ሰዎች ፣ ለፊልጵስዩስ ሰዎች ፣ ለቈላስይስ ሰዎችና ፊልሞና ለተባለ ሰው መልእክቶች ጻፈ ። (59—61 ዓ. ም.)

ከእስር ቤት ከተለቀቀ በኋላ ለሌሎች ሁለት ዓመታት ያህል የወንጌልን ሥራ በማስፋፋት እስከ እስፓኝ ድረስ እንደተጓዘ ይገመታል ። በዚሁ ወቅት ለጢሞቴዎስ የመጀመሪያውን መልእክት ጻፈ ። (61—63 ዓ. ም.)

ሁለተኛውን የጢሞቴዎስ መልእክት የጻፈው ግን ዳግመኛ ተይዞ በሮሜ በታሰረ ጊዜ ነው ። (63 ዓ. ም.)

ቅዱስ ጳውሎስ በኔሮ ጊዜ እንደተገደለ ይታመናል ። (64 ዓ. ም.)


የሐዋርያው
ጳውሎስ
መልእክቶች
ወደ ሮሜ ሰዎች
56
ሮሜ
ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
61
ፊልጵስዩስ
ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች
1
51
ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች
2
52
ተሰሎንቄ
ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች
1
53
ቆሮንቶስ
ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች
2
54
ወደ ኤፌሶን ሰዎች
61
ኤፌሶን
ወደ ቈላስይስ ሰዎች
1
61
ቈላስይስ
2
61
ወደ ፊልሞና
ገላትያ
ወደ ገላትያ ሰዎች
48
አንጾኪያ
ኢየሩሳሌም
ግብፅ

# የጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች

ስለ ጸሐፊው ፤

ሐዋርያው ጳውሎስ የወንጌልን ሥራ በእስፓኝ አገር ለመጀመር ሲሄድ የሮሜን ቤተ ክርስቲያን እግረመንገዱን ለማየት ተመኝቶ የትምህርቱን መግለጫ ከማሳሰቢያ ጭምር ላከላቸው ። መልእክቱም የተጻፈው በሦስተኛው ጉዞ ላይ በቆሮንቶስ ሳለ ነው።

የተጻፈበት ጊዜ ፤ 56 ዓ. ም.

ዓላማው ፤

ደኅንነት በእምነት መሆኑን መግለጥ ነው ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ ሮሜ 1 . 16

«በወንጌል አላፍርምና ፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው ፣ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «እምነት»

## አስተዋጽዎ


| | |
|---|---|
| መግቢያ ፤ | 1 . 1—17 |
| ስለ ኃጢአት ፤ | |
| አሕዛብ ኃጢአት ሠርተው ተረገሙ | 1 . 18—32 |
| እንዲሁም ደግሞ አይሁድ ኃጢአት ሠርተዋል | 2 . 1—3 . 8 |
| እንግዲህ ሰው ሁሉ በኃጢአት ወጥመድ ተይዞአል | 3 . 9—20 |
| ስለ ደኅንነ ት ፤ | |
| የደኅንነት መንገድና የአብራሃም አካሄድ | 3 . 21—5 . 21 |
| ደኅንነትና ጽድቅ በክርስቶስ ብቻ ይገኛል | 6 . 1—7 . 6 |
| ክርስቲያን ስለ ኦሪት ሕግ ያለው አስተያየት | 7 . 7—25 |
| በክርስቶስ ስለምናገኘው አዲስ ሕይወት | 8 . 1—39 |
| እግዚአብሔር ስለ እስራኤል ሕዝብ ያለው አስተያየት ፤ | |
| አይሁድ እምነተቢስ በመሆናቸው ለጊዜው ተነቅፈዋል | 9 . 1—33 |
| ስለ እስራኤላውያን ቀዋሚነት | 10 . 1—21 |
| የእግዚአብሔር ኪዳን ከእስራኤላውያን ጋር | 11 . 1—36 |
| ስለ ክርስቲያን አካሄድ ፤ | |
| የክርስቲያን እርምጃ | 12 . 1—13 . 14 |
| ስለ ብርቱና ስለ ደካማ ክርስቲያን | 14 . 1—15 . 13 |
| መደምደሚያ ። | 15 . 14—16 . 27 |

# መጀመሪያይቱ የጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

ስለ ደራሲው ፤

ጳውሎስ በሁለተኛው የስብከት ጉዞ ላይ ሳለ በቆሮንቶስ ለአንድ ዓመት ተኩል አቂላና ጵርስቅላ ከተባሉ ባልና ሚስት ጋር ተቀምጦ ሳለ በቆሮንቶስ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ሊቋቋም ቻለ ። ይህ መልእክት ለቆሮንቶስ ሰዎች የተጻፈው ጳውሎስ በሦስተኛው ጉዞው በኤፌሶን በተቀመጠበት ወቅት ነው ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤ 53 ዓ. ም.

ዓላማው ፤

ጳውሎስ በቆሮንቶስ አማኞች መካከል ለክርስቲያን የማይገቡ ልማዶች እንደ ገቡ ከወዳጆቹ ስለ ሰማና ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን የያዙ ደብዳቤዎች ስለ ደረሱት ፤ ይህን መልእክት ጻፈላቸው ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ 1 ቆሮንቶስ 1 · 18

«የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ፣ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «ጥበብ»

## አስተዋጽዎ

| | |
|---|---|
| መግቢያ ፤ | 1 · 1—9 |
| በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለተነሣው ክርክር ፤ | |
| ክርክሩ እንዴት እንደተነሣ | 1 · 10—4 · 13 |
| ስለ ክርክሩ በጳውሎስ የተደረገ አቤቱታ | 4 · 14—21 |
| በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተገኘው ኃጢአት ፤ | |
| ስለ ርኩሰት | 5 · 1—13 |
| እርስበርስ ስለመፈራረድ | 6 · 1—11 |
| ስለ ዝሙት | 6 · 12—20 |
| ቤተ ክርስቲያኒቱ ያቀረበቻቸው ጥያቄዎችና የጳውሎስ መልስ ፤ | |
| ስለ ክርስቲያን ጋብቻ | 7 · 1—40 |
| ስለ ጣዖት | 8 · 1—11 · 34 |
| ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት | 12 · 1—14 · 40 |
| ስለ ሞትና ትንሣኤ ፣ ስለ ጌታ ዳግም ምጽአት | 15 · 1—58 |
| ስለ ምጽዋት | 16 · 1—9 |
| መደምደሚያ ። | 16 · 10—24 |

# ሁለተኛይቱ የጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

ስለ ደራሲው ፤

ጳውሎስ የመጀመሪያውን ደብዳቤ ከጻፈ በኋላ በቆሮንቶስ የነበሩት ክርስቲያ ኖች ስሕተታቸውን እንዳላረሙ ስለተረዳ እዚያው በመሄድ ገሠጻቸው ። ከዚያም ወደ ኤፌሶን ተመልሶ ስለ ቆየ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ያለውን ሁኔታ እንዲመረ ምር ጓደኛውን ቲቶን ላከው ። ቲቶ ተመልሶ ስለ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መሻ ሻል በነገረው ጊዜ ፤ ጳውሎስ ይህን የደስታ መግለጫና ተጨማሪ ምክር ላከላቸው ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤ 54 ዓ. ም.

ዓላማው ፤

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ይህ ደብዳቤ የጳውሎስ የደስታ መግለጫ ነው ። በተጨማሪ የቆሮንቶስ ሰዎች እንደገና ወደ ኋላ እንዳይመለሱ በማስጠንቀቅ ይመክራ ቸዋል ። በመጨረሻም ጳውሎስ ለኢየሩሳሌም ችግረኞች በሚሰበስበው መዋጮ ተካ ፋዮች እንዲሆኑ ይጋብዛቸዋል ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ 2 ቆሮንቶስ 4 . 7

«ነገር ግን የኃይል ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ እቃ ውስጥ አለን ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «መተማመን»

## አስተዋጽዖ


| | |
|---|---|
| መግቢያ ፤ | 1 . 1—11 |
| ጳውሎስ ስለ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ያለው አስተያየት ፤ | |
| ወደ ቆሮንቶስ ያልተመለሰበት ምክንያት | 1 . 12—2 . 4 |
| የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በስምምነትና በአንድነት እንዲኖሩ የጳውሎስ ማሳሰቢያ | 2 . 5—13 |
| የክርስቲያን አገልግሎት ፤ | |
| ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የተቀበለው ሥልጣን | 2 . 14—4 . 6 |
| አገልግሎታችን በመከራም በደስታም ነው | 4 . 7—6 . 10 |
| ክርስቲያን ሊኖረው ስለሚገባ ፍቅርና ቅድስና | 6 . 11—7 . 16 |
| ለድሆች ምጽዋት ማከማቸት ፤ | |
| ጳውሎስ ለኢየሩሳሌም ችግረኞች አማኞች ምጽዋት እንደሰበሰበ | 8 . 1—9 . 5 |
| ስለ ክርስቲያን አሰጣጥ | 9 . 6—15 |
| የጳውሎስ አካሄድ ፤ | |
| ጳውሎስ በእግዚአብሔር ጸጋ እንጂ በራሱ አይመካም | 10 . 1—12 . 11 |
| ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የነበረው ቁጭትና ኃላፊነት | 12 . 12—13 . 10 |
| መደምደሚያ ። | 13 . 11—14 |

# የጳውሎስ መልእክት ወደ ገላትያ ሰዎች

ስለ ደራሲው ፤

ጳውሎስ በመጀመሪያው የስብከት ጉዞ በኢቆንዮ ፣ በደርቤ ፣ በአንጾኪያና በል ስጥራ ቤተ ክርስቲያኖች አቋቁሞ ስለነበር ወደ አንጾኪያ በተመለሰ ጊዜ መልእክት ጻፈላቸው ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

በሐዋርያት ሥራ 15 የተገለጠው የኢየሩሳሌም ጉባኤ ከመጀመሩ በፊት ጳው ሎስ በአንጾኪያ እንዳለ ጻፈው (48—49 ዓ. ም.) ።

ዓላማው ፤

በገላትያ ከሚገኙት ክርስቲያኖች ጥቂቶቹ ጽድቅ ለማግኘት ኦሪትን በሙሉ መጠበቅ እንደሚያስፈልግ ያስተምሩ ነበር ። ጳውሎስ ግን ጽድቅ የሚገኘው በእም ነት እንጂ ለኦሪት ሕግ በመታዘዝ እንዳይደለ በመግለጥ ይጽፍላቸዋል ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ ገላትያ 2 . 21

«የእግዚአብሔርን ጸጋ አልጥልም ፤ ጽድቅስ በሕግ በኩል ከሆነ እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «ጸጋ»

## አስተዋጽዎ


| | |
|---|---|
| መግቢያ ፤ | 1 . 1—5 |
| ስለ ጳውሎስና ፣ የእግዚአብሔር ወንጌል ስጦታ ፤ | |
| ወደ እግዚአብሔር የሚመራ አንድ አይነተኛ ወንጌል ብቻ እንዳለ | 1 . 6—10 |
| ጳውሎስ ይህን ወንጌል እንዲቀበል እግዚአብሔር እንደጠራው | 1 . 11—17 |
| በኢየሩሳሌም የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ይህን ወንጌል እንዳረጋገጡ | 1 . 18—2 . 21 |
| ስለ ደኅንነት መንገድ ፤ | |
| አብርሃም በእምነት ጽድቅን እንዳገኘ | 3 . 1—29 |
| አማኞች የእግዚአብሔር ልጆች ስለመሆናቸው | 4 . 1—7 |
| ከሕግ ባርነት ወጥተን የጸጋ ነፃነት ስለማግኘታችን | 4 . 8—20 |
| ይህ ነፃነት በአጋርና በሣራ ምሳሌ እንደተገለጠ | 4 . 21—31 |
| ስለ መንፈስ ቅዱስ ትሩፋት ፤ | |
| የመንፈስ ትሩፋት በግዝረት ወይም ሕግን በመጠበቅ አይገኝም | 5 . 1—12 |
| አማኞች በመንፈስ እንደሚመሩ | 5 . 13—26 |
| የክርስቲያኖች አንድነት | 6 . 1—18 |

# የጳውሎስ መልእክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች

**ስለ ደራሲው ፤**

ጳውሎስ ኤፌሶን በተባለ ከተማ በሁለተኛው ጉዞ ለጥቂት ጊዜ በሦስተኛውም ጉዞ ለሦስት ዓመታት ያህል ተቀምጦ ሰብኰአል ።

(የሐዋ. ሥራ 18 . 19—21 ፤ 19 . 1—20)

**የተጻፈበት ጊዜ ፤**

ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው በሮሜ ታስሮ በነበረበት ጊዜ በ61 ዓ. ም ገድም ነው ።

**ዓላማው ፤**

ይህ ደብዳቤ ለሮሜ ሰዎች የተጻፈውን መልእክት የሚመስል ሲሆን ዋና ዓላማው አይሁድና አሕዛብ ሳይለዩ አማኞች ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ መሆናቸውን መግለጥ ነው ።

**አይነተኛ ጥቅስ ፤** ኤፌሶን 2 . 18

«በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና ።»

**አይነተኛ ቃል ፤** «አንድ»

## አስተዋጽዎ

| | |
|---|---|
| **መግቢያ ፤** | 1 . 1—2 |
| **ስለ ደኅንነት ፤** | |
| ደኅንነት በጸጋ የሚገኝ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው | 1 . 3—14 |
| ስለ ኤፌሶን ሰዎችና እምነታቸው | 1 . 15—23 |
| የደኅንነት ፍሬ ቅድስና ነው | 2 . 1—10 |
| በአማኞች መሀከል ስላለው ኅብረት | 2 . 11—22 |
| **ስለ ቤተ ክርስቲያን ፤** | |
| አማኞች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነት በመኖራቸው ላላመኑት ምሳሌ ይሆናሉ | 3 . 1—13 |
| በቤተ ክርስቲያን አባሎች አካሄድ እግዚአብሔር እንዲመሰገን ይገባዋል | 3 . 14—21 |
| **ስለ ክርስቲያን ጠባይ ፤** | |
| ክርስቲያኖች ሁሉ በእምነትም ሆነ በጠባይ በአንድነት ስለመኖር | 4 . 1—16 |
| የክርስቲያን አካሄድ በፍቅርና በቅድስና መሆን አለበት | 4 . 17—5 . 20 |
| ትዳር ለያዙት ክርስቲያኖች የሚሆን ምክር | 5 . 21—6 . 4 |
| ክርስቲያንና ሥራው | 6 . 5—9 |
| ለክርስቲያን ስለተሰጠ የጦር መሣሪያ | 6 . 10—20 |
| **መደምደሚያ ።** | 6 . 21—24 |

# የጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

ስለ ደራሲው ፤

ሁለተኛውን የስብከት ጉዞ በሚያከናውንበት ጊዜ በራዕይ የተሰጠውን ትእዛዝ በመፈጸም ሐዋርያ ጳውሎስ መቄዶንን አልፎ ወደ ፊልጵስዩስ ደርሶ ልድያ የተባለች ሴት ባለችበት ስፍራ ቤተ ክርስቲያን አቋቋመ ። (የሐዋ. ሥራ 16 . 9—40)

የተጻፈበት ጊዜ ፤

ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው በሮሜ ታስሮ በነበረበት ጊዜ በ61 ዓ. ም ግድም ነው ።

ዓላማው ፤

የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን አፍሮዲጥን ለጳውሎስ እንደ ስጦታ ይዞ እንዲሄድ ላከችው (ፊልጵ 4 . 18) ። እርሱም ሮሜ እንደደረሰ በጠና ታሞ ሳይሞት ዳነ ። በተሻለውም ጊዜ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች የጻፈውን የምስጋናና የምክር ደብዳቤ ይዞ ተመለሰ ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ ፊልጵስዩስ 2 . 5

«በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «ደስታ»

## አስተዋጽዖ

መግቢያ ፤

| | |
|---|---|
| ሰላምታ | 1 . 1—2 |
| የጳውሎስ ጸሎት ለፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን | 1 . 3—11 |
| ጳውሎስ በሮሜ በታሰረበት ወቅት ወንጌል እንደተስፋፋ | 1 . 12—26 |
| ጳውሎስ አማኞችን እንዳተጋ | 1 . 27—30 |

ስለ ክርስቲያን አካሄድ ፤

| | |
|---|---|
| የክርስቲያን ምሳሌ መከተል አለብን | 2 . 1—18 |

የጳውሎስ የወደፊት አሳብ ፤

| | |
|---|---|
| ስለ ጢሞቴዎስና ስለ አፍሮዲጥ | 2 . 19—30 |
| የመንፈስ ሙላት እንዲያገኙ የጳውሎስ ምኞት | 3 . 1—21 |

መደምደሚያ ፤

| | |
|---|---|
| በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነትና ፍቅር እንዲገኝ የጳውሎስ ልመና | 4 . 1—9 |
| ቤተ ክርስቲያን ላቀረበችው ስጦታ የጳውሎስ ምስጋና | 4 . 10—19 |
| ሰላምታ ። | 4 . 20—23 |

# የጳውሎስ መልእክት ወደ ቆላስይስ ሰዎች

ስለ ደራሲው ፤

ምንም እንኳ ጳውሎስ ወደ ቈላስይስ ሄዶ ባያውቅ በሮሜ በታሰረ ጊዜ ከቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንዱ የሆነው ኤጳፍራ ሄዶ ጐብኝቶታል ። ጳውሎስ ከዚሁ ሰው ስለ ቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን እርምጃ ሰምቶ ስለነበር ይህን ደብዳቤ ጻፈላቸው ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

ጳውሎስ በሮሜ ታስሮ ሳለ በ61 ዓ. ም. ግድም ይህን መልእክት ጻፈ ።

ዓላማው ፤

ኤጳፍራ በቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን ስለተነሣው የሐሰት ትምህርት ለጳውሎስ ሲነግረው በተለይ የእግዚአብሔርን ጥበብ ትተው በሰው እውቀት መደገፋቸው አስጊ እንደሆነ አሳሰበው ። ጳውሎስም ከዚህ ሁሉ ስሕተታቸው እንዲመለሱ በማሳሰብ የጻፈውን ደብዳቤ ለፊልሞና ከተጻፈው መልእክት ጋር ከጌታው ኰብልሎ የነበረው አናሲሞስ ይዞ እንዲሄድ አደረገ ።

እይነተኛ ጥቅስ ፤ ቈላስይስ 2 . 8

«እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን ፣ እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ ፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ ። »

አይነተኛ ቃል ፤ «ምሥጢር»

## አስተዋጽዎ


ሰላምታ ፤ 1 . 1—2
ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ ምስጋናና ጸሎት እንዳቀረበ ፤ 1 . 3—14
ክርስቶስ የአዲስ ሕይወት ምንጭ ስለመሆኑ ፤
ሰው በክርስቶስ ተፈጥሮ በክርስቶስ ደኅንነት ያገኛል 1 . 15—2 . 5
የአማኞች ሕይወት በክርስቶስ የተመሠረተ ነው 2 . 6—15
ለክርስቲያን የተሰጠ ነፃነት 2 . 16—23
ሰው ለኃጢአት ከሞተ በኋላ ስላለው አዲስ ሕይወት 3 . 1—11
የክርስቲያን አካሄድ ፤
ስለ ክርስቲያን አንድነትና ፍቅር 3 . 12—17
ስለ ቤተሰብ ኑሮ 3 . 18—21
አማኞችና ሥራቸው 3 . 22—4 . 6
መደምደሚያ ። 4 . 7—18

# መጀመሪያይቱ የጳውሎስ መልእክት
# ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

ስለ ደራሲው ፤

ሐዋርያው ጳውሎስ በሁለተኛው የስብከት ጉዞው ላይ ሳለ ወደ ተሰሎንቄ ደርሶ አስተምሮ ስለነበር ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተ ። (የሐዋ. ሥራ 17.1—9)

የተጻፈበት ጊዜ ፤

ጳውሎስ በሁለተኛው ጉዞው ላይ ሳለ ከተሰሎንቄ ተነሥቶ ወደ ቆሮንቶስ ሄዶ ስለነበር እዚያው ሆኖ በ51 ዓ. ም. ግድም ይህን መልእክት ለተሰሎንቄ ሰዎች ጻፈ ። (የሐዋ. ሥራ 17.1—17)

ዓላማው ፤

በተሰሎንቄ ሳለ ጳውሎስ በድንጋይ ተወግሮ ስለነበር ሕይወቱን ለማዳን በፍ ጥነት አመለጠ ። ይሁን እንጂ ጥቂት እንደቆየ ጢሞቴዎስን በመላክ ስለ እምነታ ቸው እድገት ለማወቅ ችሎአል (የሐዋ. ሥራ 18.1—5) ። ጢሞቴዎስ በተመለሰ ጊዜ ስለ ተሰሎንቄ ሰዎች መልካም ወሬ አምጥቶለት ስለነበር ጳውሎስ የደስታ ውን መግለጫና ስለ ክርስቲያን ሃይማኖት በተለይም ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መም ጣት የያዘ ደብዳቤ ላከላቸው ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ 1 ተሰሎንቄ 1.5

«ወንጌላችን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «ጽኑ»

## አስተዋጽዎ


መግቢያ ፤ 1.1

ጳውሎስና የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ፤

- ወንጌሉን በሰሙ ጊዜ በደስታ እንደተቀበሉ 1.2—10
- ጳውሎስ በተሰሎንቄ ሳለ የነበረው ጠባይ 2.1—16
- ጳውሎስ ተሰሎንቄን በተወ ጊዜ የነበረው ሥጋት 2.17—3.13

የክርስትና ትምህርት ፤

- ስለ ቅድስና 4.1—12
- ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት 4.13—18
- የጌታን መምጣት በመጠበቅ ስለ መትጋት 5.1—11
- የክርስቲያን ኑሮ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ 5.12—24

መደምደሚያ ። 5.25—28

# ሁለተኛይቱ የጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

ስለ ደራሲው ፤

ይህ መልእክት እንደ መጀመሪያው መልእክት ከቆሮንቶስ ከተማ የተጻፈ ሲሆን ደራሲውም ሐዋርያ ጳውሎስ ነው ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤ በ52 ዓ. ም. ግድም ።

ዓላማው ፤

የመጀመሪያው የጳውሎስ መልእክት በተሰሎንቄ በተነበበ ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባሎች የጌታ መመለስ ከተቃረበ ሥራም አያስፈልግ በሚል አሳብ በስንፍና ለመቀመጥ አቀዱ ። ጳውሎስ ይህን በመስማቱ ጌታን የሚጠብቁት በትጋት እንጂ በስንፍና እንዳልሆነ በማስገንዘብ እንደገና ጻፈላቸው ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ 2 ተሰሎንቄ 3 . 13

«እናንተ ግን ወንድሞች ሆይ መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «ትዕግሥት»

## አስተዋጽዎ

| | |
|---|---|
| ሰላምታ ፤ | 1 . 1—2 |
| ጳውሎስ ስለ እምነታቸውና ስለ ትዕግሥታቸው እንዳመሰገናቸው ፤ | 1 . 3—4 |
| ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ፤ | |
| ክርስቶስ በዓለም ላይ ሊፈርድ ተመልሶ ይመጣል | 1 . 5—12 |
| የጌታ አመጣጥ | 2 . 1—12 |
| ስለ ጸሎት ፤ | |
| ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች ያደረገው ጸሎት | 2 . 13—17 |
| ጳውሎስ ለእርሱ እንዲጸልዩ እንደለመናቸው | 3 . 1—2 |
| ለቅድስና ሕይወት ስለመጣጣር ፤ | 3 . 3—15 |
| መደምደሚያ ። | 3 . 16—18 |

# መጀመሪያይቱ የጳውሎስ መልእክት ወደ ጢሞቴዎስ

ስለ ደራሲው ፤

በመጀመሪያው የስብከት ጉዞ ጳውሎስ በልስጥራ ወንጌልን በማስተማር ቤተ ክርስቲያን አቋቁሞ ስለነበር ፤ በሁለተኛው ጉዞ ወደዚህ ሲመለስ በሥራው እን ዲረዳው ጢሞቴዎስን ይዞ ጉዞውን ቀጠለ (የሐዋ. 11 . 1—3) ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

ጳውሎስ በሮሜ ለሁለት ዓመታት ታስሮ እንደተለቀቀ ሲታወስ በዚያኑ ጊዜ ይህን መልእክት ለጢሞቴዎስ ጽፎለታል (ከ61—62 ዓ. ም. ግድም) ።

ዓላማው ፤

ጳውሎስ ከሮሜ እስር ቤት እንደወጣ ፥ የስብከት ሥራውን ቀጥሎ ስለነበር ኤፌሶንን በጐበኘበት ወቅት በዚያ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን እንዲያበረታታ ጢሞ ቴዎስን ትቶት ሄደ (1 ጢሞ. 1 . 3) ። በዚህ መልእክት ጢሞቴዎስ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ያለበትን ኃላፊነት በማስገንዘብና ፤ አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮችን በመስጠት ይጽፍለታል ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ 1 ጢሞቴዎስ 4 . 12

«በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑት ምሳሌ ሁን ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «አስተምር»

## አስተዋጽዎ

| | |
|---|---|
| መግቢያ ፤ | 1 . 1—2 |
| ጢሞቴዎስ የቤተ ክርስቲያን አባሎችን እንዲያስተምር እንደታዘዘ ፤ | 1 . 3—20 |
| የትምህርት አይነቶች ፤ | |
| ስለ ጸሎት | 2 . 1—8 |
| ስለ ሴቶች ይዞታና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚያደርጉት ሁኔታ | 2 . 9—15 |
| ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች | 3 . 1—16 |
| አማኞች ስለሚፈጽሙት ሥነ ሥርዓት | 4 . 1—16 |
| ስለ ባልቴቶችና ስለ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች | 5 . 1—25 |
| ስለ ባሪያዎች | 6 . 1—2 |
| የጳውሎስ ምክር ስለ ሐብታሞችና ስለ ሐብት | 6 . 3—10 |
| መደምደሚያ ። | 6 . 11—21 |

# ሁለተኛይቱ የጳውሎስ መልእክት ወደ ጢሞቴዎስ

ስለ ጸሐፊው ፤

ጳውሎስ ለሁለት ዓመታት በሮሜ ታስሮ ከተፈታ በኋላ ለሁለት ዓመታት እየተዘዋወረ ወንጌልን አስተምሮአል ። ከዚያ በኋላ እንደገና ተይዞ በሮሜ ታስሮ ስለነበር ፡ ከዚያው ሳለ ይህችን መልእክት ለጢሞቴዎስ ጽፎአል ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤ 63 ዓ. ም.

ዓላማው ፤

ሁለተኛ በሮሜ በታሰረ ጊዜ መሞቻው እንደቀረበ በመረዳቱ ለጢሞቴዎስ ልዩ ልዩ ምክሮችን በመስጠት ሊያየውም እንደናፈቀ ያመለክተዋል ። (2 ጢሞ. 1 · 4)

አይነተኛ ጥቅስ ፤ 2 ጢሞቴዎስ 4 · 7

«መልካሙን ገድል ተጋድልሁ ፡ ሩጫውን ጨርሻለሁ ፡ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «በርታ»

## አስተዋጽዎ

| | |
|---|---|
| ሰላምታ ፤ | 1 · 1—2 |
| ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የነበረው ፍቅር ፤ | 1 · 3—14 |
| ስለ ጳውሎስ ሥቃይ ፡ ስደትና ትዕግሥት ፤ | 1 · 15—2 · 19 |
| ለጢሞቴዎስ ስለ ንጹሕ አኗኗር የተሰጠ ምክር ፤ | 2 · 20—26 |
| ስለ ዓለም ፍጻሜ ፤ | 3 · 1—4 · 5 |
| ጳውሎስ ወደ ሞት ቀርቦ የተደረገ ጸሎት ፤ | 4 · 6—18 |
| መደምደሚያ ። | 4 · 19—22 |

# የጳውሎስ መልእክት ወደ ቲቶ

ስለ ደራሲው ፤

ጳውሎስ ስለ ቲቶ በሚያወሳበት ጊዜ ልጄ እያለ ስለሚጠራው ቲቶን ወደ ክርስትና ሃይማኖት የመራው እርሱ እንደሆነ ይገመታል (ቲቶ 1 · 4)። ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ጉባኤ በሄደ ጊዜና በሁለተኛውና በሦስተኛው የስብከት ጉዞው ቲቶን እንዳስከተለው ታውቆአል ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

ጳውሎስ ይህንን መልእክት ለቲቶ የጻፈው ከእስራቱ ከተፈታ በኋላ ስለነ በር ጊዜው በ62—63 ዓ. ም. ግድም ነው ።

ዓላማው ፤

ጳውሎስ ከእስራቱ እንደተፈታ የስብከት ጉዞውን በመቀጠል ወደ ቁርጤስ ሄደ ። ከዚያም ጉዞውን በማራዘም ወደ ሌሎች አገሮች ሄዶ ስለነበር ቲቶ ወደ ኋላ ቀርቶ እንዲያስተምር አዞት ነበር ። ይህም መልእክት ቲቶ በሥራውም ሆነ በምስክ ርነቱ እንዲበረታታ ለማድረግ የታቀደ ነው ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ ቲቶ 1 · 31

«በሃይማኖት ጤናሞች እንዲሆኑ በብርቱ ውቀሳቸው ።»

ዓይነተኛ ቃል ፤ «ምክር»

አስተዋጽዎ

| | |
|---|---|
| ሰላምታ ፤ | 1 · 1—4 |
| ስለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አመራረጥ ፤ | 1 · 5—9 |
| ስለ ሐሰተኞች አስተማሪዎች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ፤ | 1 · 10—16 |
| ለሽማግሌዎች ፣ ለወጣቶችና ለአሽከሮች የተሰጠ ምክር ፤ | 2 · 1—15 |
| በእግዚአብሔር ጸጋ ከዳንን በኋላ ስለሚኖረን አዲስ ሕይወት ፤ | 3 · 1—11 |
| መደምደሚያ ። | 3 · 12—15 |

# የጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልሞና

ስለ ደራሲው ፤

ይህን መልእክት ፊልሞና ለተባለ በቈላስይስ ለሚኖር ሰው የጻፈው ሐዋር ያው ጳውሎስ ነው ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

ጳውሎስ በሮሜ ታስሮ ሳለ ለቈላስይስ ሰዎች ከጻፈው ደብዳቤ ጋር ይህንንም አብሮ ጻፈ (በ62—63 ዓ. ም. )።

ዓላማው ፤

አናሲሞስ የተባለ ባሪያ ፊልሞና ከተባለ ጌታው ኰብልሎ ወደ ሮሜ በመሄድ ጳውሎስን እስር ቤት አገኘው ። ከዚያም ሳለ ክርስቲያን ሆነ ። ጳውሎስ ወደ ጌታው ወደ ፊልሞና በላከው ደብዳቤ ውስጥ ይቅርታ እንዲያደርግለት ያሳስበዋል ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ ቍጥር 10

«ስለ ልጁ ስለ አናሲሞስ እለምንሃለሁ ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «ወንድም»

አስተዋጽዎ


| | |
|---|---|
| ሰላምታ ፤ | 1—7 |
| ስለ አናሲሞስ የተሰጠ ማሳሰቢያ ፤ | 8—21 |
| መደምደሚያ ። | 22—25 |


## ዕብራውያን

ደራሲው ፤

የዚህ መልእክት ጸሐፊ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሆነ ይገመታል ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤ 64 ዓ. ም. ግድም

ዓላማው ፤

ከአይሁድ ወገን ወደ ክርስትና ከተመለሱት ጥቂቶቹ የብሉይ ኪዳንን ሥርዓት መከተል አስፈላጊ መስሎ ታይቶአቸው ነበር ። ነገር ግን ክርስቶስ የብሉይ ኪዳንን ክህነትና መሥዋዕት እንደፈጸመ በዚህ መልእክት ተገልጦአል ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ ዕብራውያን 3 . 1

«የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ክህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «ይበልጣል»

አስተዋጽዎ


| | |
|---|---|
| ክርስቶስ ከመላእክት በላይ ነው ፤ | 1 . 1—2 . 18 |
| ከሙሴ በመብለጡ ፣ የሚሰጠውም እረፍት እርሱ ከሰጠው የበለጠ ነው ፤ | 3 . 1—4 . 13 |
| የእርሱ ክህነት ከቀድሞው ክህነት የበለጠ ነው ፤ | 4 . 14—5 . 14 |
| ደራሲው በመንፈስ እንዲጸኑ ሲጠራቸው ፤ | 6 . 1—20 |
| ክርስቶስ ለአማኞች ሊቀ ካህን ስለመሆኑ ፤ | 7 . 1—8 . 13 |
| በሊቀ ክህናቱ ያቀረበው መሥዋዕት ፤ | 9 . 1—10 . 39 |
| በብሉይ ኪዳን ስለተገኙ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ፤ | 11 . 1—40 |
| በአሁኑ ጊዜ ለክርስቲያን ስለተሰጠው አገልግሎት ፤ | 12 . 1—13 . 21 |
| መደምደሚያ ። | 13 . 22—25 |

# መጀመሪያይቱ የጴጥሮስ መልእክት

ስለ ደራሲው ፤

ሐዋርያው ጴጥሮስ ይህን ደብዳቤ በጻፈበት ወቅት ሮሜ እንደነበረ ይታመናል። ነገር ግን የሮሜ መንግሥት በአማኞች ላይ ሊያደርስባቸው ያቀደውን መከራና ስደት በማወቁ ፣ በተዘዋዋሪ አነጋገር ሮሜን ባቢሎን በማለት ይጠቅሳል ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

በኔሮ አነሣሺነት የተደረገው ስደት ሳይጀመር በ63—64 ዓ. ም. ።

ዓላማው ፤

እስጢፋኖስ በተገደለበት ወቅት ብዙ ክርስቲያኖች ተመሳሳይ ድርጊት እንዳይፈጸምባቸው በያለበት ተበታተኑ (የሐዋ. 6.7)። በሮሜ ውስጥ የተነሣው ስደት ወደየቦታው መሰራጨቱ እንደማይቀር በማሰብ ጴጥሮስ ለእነዚህ ክርስቲያኖች ማስጠንቀቂያ ላከላቸው ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ 1 ጴጥሮስ 4.16

«ክርስቲያን እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል ስለዚህ ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «መከራ»

## አስተዋጽዖ


| | |
|---|---|
| መግቢያ ፤ | 1.1—2 |
| በእግዚአብሔር ስለተዘጋጀው የደኅንነት መንገድ ፤ | 1.3—12 |
| ክርስቲያኖች ሁሉ ለቅድስና ስለመጠራታቸው ፤ | 1.15—2.10 |
| የክርስቲያን ተግባር ፤ | |
| ለመንግሥት የሚፈጽመው ተግባር | 2.11—17 |
| ሎሌዎች ወይም አሽከሮች ሊፈጽሙት የሚገባ ተግባር | 2.18—25 |
| ስለ ቤተ ሰብ ኑሮ | 3.1—7 |
| አማኞች በቤተ ክርስቲያን ያላቸው ተግባር | 3.8—12 |
| መከራና ስደት ስለመቀበል ፤ | 3.13—4.19 |
| የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት ፤ | 5.1—11 |
| መደምደሚያ ። | 5.12—14 |

# ሁለተኛይቱ የጴጥሮስ መልእክት

ስለ ደራሲው ፤

ጴጥሮስ የመጀመሪያ መልእክቱን በስደት ለተበታተኑት ክርስቲያኖች እንደ ጻፈ ሲታወስ ሁለተኛው መልእክቱም ለነዚያው ሰዎች በድጋሚ የተጻፈ ነው ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

ጴጥሮስ በዚህ መልእክቱ በሮሜ ገዥ በኔሮ ትዕዛዝ ለመሞት መዘጋጀቱን ስለሚገልጽ ይህ መልእክት የተጻፈው በ68 ዓ. ም. እንደሆነ ይገመታል (2 ጴጥ. 1 . 14—15) ።

ዓላማው ፤

ይህ መልእክት ሐሰተኞች አስተማሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለተነሡ አማኞች ከእነርሱ መጠንቀቅ እንዳለባቸውና ባይጠነቀቁ ግን ለሐሰተኞች የተዘጋጀው ቅጣት እንደሚደርስባቸው ያስገነዝባቸዋል ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ 2 ጴጥሮስ 2 . 1

«በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ ፤ እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፉ ኑፋቄን አሹልከው ያገባሉ ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «ሐሰት»

## አስተዋጽዎ


| | |
|---|---|
| መግቢያ ፤ | 1 . 1 |
| የክርስቲያን አስተዳደግ ፤ | 1 . 2—11 |
| ጴጥሮስ ከክርስቶስ የተማረውን ሰብከአል ፤ | 1 . 12—21 |
| ስለ ሐሰተኞች አስተማሪዎች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ፤ | 2 . 1—22 |
| ስለ ጌታ ዳግመኛ መምጣት ፤ | 3 . 1—13 |
| መደምደሚያ ። | 3 . 14—18 |

# መጀመሪያይቱ የዮሐንስ መልእክት

ስለ ደራሲው ፤

ከኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አንዱ የነበረው ሐዋርያ ዮሐንስ ፣ በ70 ዓ. ም. ኢየሩሳሌም በሮሜ ጦር ሠራዊት ስትወረር አማኞች በተበታተኑ ጊዜ እርሱም ወደ ኤፌሶን እንደሄደ ይታመናል ። ከዚያም ሆኖ ይህን መልእክት በኤፌሶን ዙሪያ ለነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ጽፎአል ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

ዶሚትየን የተባለው የሮሜ ገዥ በቤተ ክርስቲያን ላይ ስደት ባስነሣበት ወቅት በ80—90 ዓ. ም. ተጻፈ ።

ዓላማው ፤

በክርስቲያን ሃይማኖት መሠረታዊ የሆኑ ትምህርቶችን የካዱ ሐሰተኞች አስተማሪዎች በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ተነሥተው ነበር ። ዮሐንስ ግን ክርስቶስ ሲናገራቸው የሰማውንና ሲያደርጋቸው ያየውን ሁሉ በመግለጽ አማኞች በእምነታቸው እንዲጠነክሩ ያሳስባቸዋል ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ 1 ዮሐንስ 1 . 6

«ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትም አናደርግም ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «ብርሃን»

አስተዋጽዎ

| | |
|---|---|
| መግቢያ ፤ | 1 . 1—4 |
| ክርስቲያን እግዚአብሔርን እንደማመኑ መጠን በብርሃን መመላለስ አለበት | 1 . 5—2 . 17 |
| ስለ ከሐዲዎች ፤ | 2 . 18—29 |
| አማኞች የእግዚአብሔር ልጆች ስለመሆናቸው ፤ | 3 . 1—4 . 6 |
| እግዚአብሔር ለእኛ ስላለው ፍቅር ፤ | 4 . 7—5 . 12 |
| መደምደሚያ ። | 5 . 13—21 |

# ሁለተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት

ስለ ደራሲው ፤

ደራሲው ሐዋርያው ዮሐንስ ነው ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

ይህ መልእክት እንደ መጀመሪያው መልእክት በ80—90 ዓ. ም. ተጽፎአል ።

ዓላማው ፤

ዮሐንስ ይህን ደብዳቤ የጻፈው ለአንዲት ክርስቲያን ሴት ሲሆን የሰጣት ማሳሰቢያ ከሐሰተኞች አስተማሪዎች እንድትጠነቀቅ ነው ። አንዳንዶች ሰዎች ግን «እመቤትን ከልጆችዋ» ጋር የሚጠቅሰው ስለ ሰው ሳይሆን ስለ ቤተ ክርስቲያንና እርሱዋም ስላፈራቻቸው አማኞች እንደሆነ ያምናሉ ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ ቁጥር 7

«ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ገብተዋልና እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የማያምኑ ናቸው ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «እውነት»

አስተዋጽዎ

| | |
|---|---|
| መግቢያ ፤ | 1—3 |
| ስለ እውነተኛና ስለ ሐሰተኛ አስተማሪ ፤ | 4—11 |
| መደምደሚያ ። | 12—13 |

# ሦስተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት

ስለ ደራሲው ፤ ደራሲው ሐዋርያው ዮሐንስ ነው ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

የቀሩት የዮሐንስ መልእክቶች በተጻፉበት ጊዜ በ80—90 ዓ. ም. ።

ዓላማው ፤

ታማኙ የወንጌል አስተማሪ በዲዮጥራጢስ በተነቀፈ ጊዜ ዮሐንስ ጉዳዩን በመቃወም ለጋይዮስ ጻፈለት ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ ቁጥር 9

«ዋናቸው ሊሆን የሚወድ ዲዮጥራጢስ አይቀበለንም ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «ተቀበል»

አስተዋጽዎ

| | |
|---|---|
| መግቢያ ፤ | 1—4 |
| ስለ ማስተናገድ ፤ | 5—8 |
| ስለ ዲዮጥራጢስ ኩራት ፤ | 9—12 |
| መደምደሚያ ። | 13—15 |

# የሐዋርያው የያዕቆብ መልእክት

ስለ ደራሲው ፤

በ ምዕራፍ አንድ ቍጥር አንድ እንደተገለጠው መልእክቱን የጻፈው የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ያዕቆብ መሆኑን እናገኛለን ። የዮሐንስ ወንድም የነበረው ሐዋርያው ያዕቆብ በ44 ዓ. ም. በሄሮድስ እንደተገደለ ሲታወስ ፤ የዚህ መልእክት ደራሲ የሆ ነው ያዕቆብ ግን በማቴዎስ 13 . 55 እንደተገለጠው የክርስቶስ ወንድም መሆኑ የተ ረጋገጠ ነው ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

ያዕቆብ በ62 ዓ. ም. በሊቀ ካህኑ በአናንያ ትዕዛዝ በድንጋይ ስለሞተ ፤ ይህ መልእክት የተጻፈው በ55—60 ዓ. ም. ግድም እንደሆነ ይገመታል ።

ዓላማው ፤

ያዕቆብ ይህን ደብዳቤ የጻፈው ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ከጻፈላቸው በኋላ በግምት አሥር ዓመታት ያህል ቆይቶ ነው ። ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የጸጋን ምሥ ጢር በማፍታታት ሲገልጽላቸው «ደኅንነት በእምነት እንደሆነና ይኸውም የእግዚአ ብሔር ስጦታ እንደሆነ» አስገንዝቦአቸዋል ። ስለሆነም አንዳንድ ክርስቲያኖች በመሳ ሳት «መልካም ጠባይና በጐ አድራጐት አያስፈልጉም» በማለት ሕይወታቸውን አበ ላሽተውት ስለነበር ፤ ያዕቆብ መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ሊያደርገው ስለሚችል ሥራ በማስረዳት ይጽፍላቸዋል ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ ያዕቆብ 2 . 17

«እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «ሥራ»

## አስተዋጽዖ


| | |
|---|---|
| መግቢያ ፤ | 1 . 1 |
| የክርስቲያን እምነት የሚፈተንበት ምክንያቶች ፤ | 1 . 2—27 |
| ሃይማኖት አድሎ የሌለበት ነው ፤ | 2 . 1—13 |
| የእምነት መግለጫ ፤ | 2 . 14—26 |
| እምነትና የክርስቲያን አካሄድ ፤ | 3 . 1—5 . 6 |
| እምነትና የክርስቲያን ትዕግሥት ፤ | 5 . 7—12 |
| በእምነት ስለመጸለይ ። | 5 . 13—20 |

# የያዕቆብ ወንድም የይሁዳ መልእክት

ስለ ጸሐፊው ፤

የዚህ መልእክት ደራሲ የሆነው ይሁዳ የያዕቆብና «የክርስቶስ ወንድም» እን ደነበረ ከማቴዎስ 13.55 እንረዳለን ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

በ70—80 ዓ. ም. ግድም ።

ዓላማው ፤

እስጢፋኖስ ፣ ያዕቆብ ፣ ጳውሎስ ፣ ጴጥሮስና ሌሎችም በሰማዕታትነት ከሞቱ በኋላ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ክርስቶስን እየካዱ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ተነሥ ተው ነበር ። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ቀድሞ ለኢየሱስ የነበራትን ፍቅር እንዳትተ ውና ሐዋርያት ያስተማሩዋትንም ትክክለኛ እምነት እንዳትጥል በማሳሰብ ይሁዳ ይህን መልእክት ጻፈ ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ ቊጥር 17

«በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ቀድሞ የተነገረውን ቃል አስቡ ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «አስቡ»

## አስተዋጽዎ


| | |
|---|---|
| መግቢያ ፤ | 1—2 |
| ስለ ሐሰተኞች አስተማሪዎች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ፤ | 3—16 |
| ይሁዳ አማኞች ሁሉ ወደ ቅድስና እንዲመለሱ እንዳሳሰበ ፤ | 17—23 |
| መደምደሚያ ። | 24—25 |

# የዮሐንስ ራእይ

ስለ ደራሲው ፤

ይህን መልእክት ሐዋርያው ዮሐንስ የጻፈው ፍጥሞ በምትባል ደሴት ላይ በግዞት ሳለ ነው ።

የተጻፈበት ጊዜ ፤

ዮሐንስ ታስሮ የነበረው ወይም ኔሮ ወይም ዶሚትየን በተባሉ የሮሜ ገዥ ዎች ትዕዛዝ ስለነበር ፥ መልእክቱ የተጻፈው ወይም በ60—70 ዓ. ም. ግድም ወይም በ85—95 ዓ. ም. ግድም ሳይሆን አይቀርም ።

ዓላማው ፤

ዮሐንስ ወደፊት ስለሚሆኑት ነገሮች ራእይ ተገልጦለት ስለነበር ፤ ይህንኑ ራእይ በእስያ ለሚገኙት ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ላከላቸው ።

አይነተኛ ጥቅስ ፤ የዮሐንስ ራእይ 2 . 29

«መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ ።»

አይነተኛ ቃል ፤ «የእግዚአብሔር በግ»

## አስተዋጽዎ


| | |
|---|---|
| መግቢያ ፤ | 1 . 1—18 |
| ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ መልእክቶች ፤ | 1 . 9—3 . 22 |
| ስለ እግዚአብሔር ዙፋን የታየ ራእይ ፤ | 4 . 1—5 . 14 |
| ስለ ሰባቱ ማሕተሞች ፤ | 6 . 1—7 . 17 |
| ስለ ሰባቱ መለከቶች ፤ | 8 . 1—11 . 19 |
| ስለ ዘንዶውና አውሬው ፤ | 12 . 1—13 . 18 |
| ስለ አጫጁ ፤ | 14 . 1—20 |
| ስለ ሰባቱ መላእክትና ሰባቱ ጽዋዎች ፤ | 15 . 1—16 . 21 |
| ስለ ባቢሎን ውድቀት ፤ | 17 . 1—19 . 21 |
| ስለ መንግሥተ ሰማያትና ስለ ገሃነመ እሳት ፤ | 20 . 1—22 . 5 |
| መደምደሚያ ። | 22 . 6—21 |

# የዮሐንስ ራእይ


ጴርጋሞን
ትያጥሮን
ሰርዴስ
ሰምርኔስ
ኤፌሶን
ፊልድ
ልፍያ
ሎዶቅያ
ፍጥሞ
አንጾኪያ
ታላቁ ባሕር
ኢየሩሳሌም
ግብፅ


ቅድስት ሐገር
ገ ሊ ላ
ቅፍርናሆም
የገሊላ ባሕር
ቃና
ናዝሬት
ታላቁ ባሕር
ሰ ማ ር ያ
ሰማርያ
ሲካር
የዮርዳኖስ ወንዝ
ይ ሁ ዳ
ኢያሪኮ
ኢማሁስ
ኢየሩሳሌም
ቤተ ልሔም
የጨው ባሕር